# የምፅዓቱ የምሥራች

መፅሐፍ ቅዱስ
Holy Bible

ሃያ አምስተኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ ልዩ ዕትም

ቅጽ 75 ቁ 6 (894)


**“እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ እወቁ”**

ማቴ 24:33

## የጌታ ዳግም ምጽአት ምልክቶች

በዕብራውያን መልእክት ምዕ.10:25“ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ ይህን አድርጉ” ተብሎ የተፃፈው የጌታን ዳግም ምጽአት ለማሳሰብ ነው፡፡

ከጌታ ዳግም ምጽአት በፊት የሚከሰቱ ነገሮችና ወቅቱን በትክክል እንድናውቅ ቅዱስ ቃሉ ያሳስበናል፡፡ እነዚህ ምልክቶች ምንድን ናቸው? በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት የምንጠብቃቸው ነገሮች የትኞቹ ይሆኑ?

ከነዚህ ምልክቶች ውስጥ ብዙዎቹ እየታዩ ሲሆን ከእነርሱም ውስጥ እንዳንዶቾቹን መቀበልና ማስተናገድ አስቸጋሪ እየሆነ ነው፡፡

እነዚህን የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች በሚገባ ለማወቅና በአግባቡም ለመቋቋም እንዲቻል በ5 ዋና ዋና ክፍሎች እንመለከታለን፡፡

### የተፈጥሮ ምልክቶች

“ታላቅም የምድር መናወጥና በልዩ ልዩ ስፍራ ቸነፈር ረብም ይሆናል፤ የሚያስፈራም ነገር ከሰማይም ታላቅ ምልክት ይሆናል” (ሉቃስ 21:11)

በብዙዎች በሚያምኑት ሳይቀር እነዚህ ምልክቶች የተለመዱ መሆናቸው ቢነገርም ቃሉ የምጥ ጣር ጅማሬ ይላቸዋል(ማቴ. 24:8)

### የማህበረሰብ ምልክቶች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበትን ጊዜ ከኖህ ዘመን ጋር በማመሳሰል አቅርቦታል(ማቴ.24:37) በብሉይ ኪዳን የኖህ ዘመን በታሪክ እጅግ የከፋው እንደነበር ተገልጧል፡፡ በኖህ ዘመን የሰዎች ልብ በክፉው ኃጢአት የተሞላ ነበር(ዘፍ. 6:5-13)

በአዲስ ኪዳን በሮሜ መልዕክት 1:18-32 ማህበረሰቡ በሥነ ምግባር የተበላሸ ኃጢአተኛ ትውልድ መሆኑ ተብራርቷል፡፡ “የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው”

### መንፈሳዊ ምልክቶች

አያሌ በጎና መጥፎ መንፈሳዊ ምልክቶች በመታየት ላይ ናቸው፡፡ መጥፎዎቹ መንፈሳዊ ምልክቶች በ2 ጢሞቴዎስ 4:3 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

ምልክቶች በ2 ጢሞቴዎስ 4፡3 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

“ህይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና ነገር ግን ጆሮዎቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ”

ይህ አባባል አሁን ትክክል ነውን? አዎን! በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ ብዙዎች ለራሳቸው ብቻ የሚመች ስብከት መስማት የሚፈልጉበት ጤናማ የህይወት የክርስትና ቃልን መስማት የማይፈልጉበት ዘመን ላይ ነን፡፡ ብዙዎች ዋና ዋና አብያተ ክርስቲያናት የመፅሀፍ ቅዱስን የበላይነት ክደዋል፡፡ በትክክለኛው የክርስትና ወንጌል ቦታ የጤናና የብልፅግናን ወንጌል የሚሰብኩም ተበራክተዋል፡፡ አንዳንዶቹም የስነአዕምሮ ሰባኪ በመሆን ሰዎችን የሚያድነውን የወንጌልን ስብከት ትተዋል፡፡

እውነተኛ ሰባኪዎችና ሰሚዎቻቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን እንደከፈተላቸው እንደቤሪያ ሰዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ (ሐዋ. 17፡10)

እውነተኛ ክርስቲያኖች የመስበክ ነፃነታቸው የመዐለይ መብታቸው በትምህርት ቤትና በአደባባይ እየተሰከለከለ ይገኛል፡፡ በእውነተኛ ክርስቲያኖች ላይ የዘመኑ ሚዲያ እየተሳለቀባቸው ነው፡፡

ሰይጣን የወንጌሉን ሀይል ስለሚያውቅና ትክክለኛ የወንጌል ሰባኪዎችን ከመድረክ እያራቀ አታላዮችን እያበራከተ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ገን በበጎ መልኩ ትክክለኛውን የወንጌል ቃል በእውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች እየተመሰከረና እየተሰበከ የትንቢት ቃሉ በመፈፀም ላይ ነው፡፡ (ማቴ. 24፡14)

ለዘመኑ እውነተኛ ክርስቲያኖች ትክክለኛ ምሳሌ የክርስትናን ቃል በመስበካቸው የታሰሩና የተገደሉ የጥንት ነብያትና ክስቲያኖች ናቸው፡፡ (ዳንኤል 12፡4) (ሐዋ. 5፡17)

## የዓለም ፖለቲካ ምልክቶች

“ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፡፡ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሳልና” (ማቴ. 24፡6)

ባለፉት ሃያ ዓመታት በሁሉም ሀገሮች መንግስታዊና ፖለቲካዊ ችግሮች እየከፉ ሄደዋል፡፡ ከመካከለኛ ምስራቅ አንስቶ እስከ ደቡብ አሜሪካ ታይተው የማይታወቁ ፖለቲካዊና መንግስታዊ ግጭቶችና ፍጥጫዎች እየታዩ በመሆኑ የመጨረሻውን ዘመን ምልክቶች እያሳዩን ነው፡፡

## የእስራኤል ምልክት

“የምድርም አሕዛብ ሁሉ በላይዎ ላይ ይከማቻሉ” (ዘካ. 12፡3) እስራኤል ተብሎ የሚጠራው ሕዝብ በመፅሐፍ ቅዱስ ለአዲሷ እስራኤል በክርስትና ላመኑት የተሰጠ ስም ነው ፡፡ በዚህም የማያምኑት ወይም አህዛብ ምን ያህል በሚያምኑት ላይ ተገዳዳሪ ሆነው እንደተነሱ በየቀኑ የምናየው ነው፡፡

በተጨማሪም የተስፋ ምድር ሆና ለተበተኑት እስራኤሎች የተዘጋጀችው እስራኤልን የተነሱባት ክፉ አሸባሪዎችና ተቃዋሚዎችን በንፅፅር ከአዲሱ እስራኤል ጋር በማነፃፀር ምልክቶቹን መረዳት እንችላለን፡፡

እንግዲህ እነዚህ የጌታ ምፅአት ምልክቶችን እያየን እኛ ልጆቹ ይበልጥ ልንተጋና ወንጌሉን ልንዘራ ከክፉ ልንጠበቅ የግድ ያስፈልገናል፡፡

## የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ሰዓት እየደወለ ነው!

የዚህ እትም የምዕተ፡ የምሥራች የጌታ ዳግም ምፅአት ላይ ያተኩራል፡፡

የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ የሆነው እስራኤል ህልውና ማግኘት በእስራኤል ላይ ብዙ ተቃዋሚ እንዳስነሳ በአዲሱ እስራኤል በሆነው እየሱስ ክርስቶስን ብቻ ጌታ ባደረገው የክርስቲያን ማህበረሰብ ላይ በስውርም ሆነ በግልፅ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ተቃውሞ ብሷል፡፡

የጥፋት ልጅ የተባለው ሐሰተኛ ክርስቶስ በቅዱስ ቃሉ እንደተፃፈ በልዩ ልዩ መንገድ እውነተኛ ክርስቲያኖችን በመቃወምና የስም ክርስቲያኖችን በማሳት ስራውን የቀጠለ ሲሆን በመጨረሻም አውሬው ሊገለጥ የግድ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር ደግሞ የመጨረሻ ዘመን ትንቢት እግዚአብሔር እንደ አጥንት በደረቀው የህዝቦቹ ጉባኤና ህብረት ላይ መንፈሱን ይልካል(ሕዝ. 37፡8)

ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ ብሎ ጌታ እንዳስተማረው የአሕዛብ ዘመን እስኪፈፀም ድረስ ኢየሩሳሌም በአህዛብ የተረገጠች ትሆናለች የሚለው የትንቢት ቃል እየታየ ነው፡፡(ማቴ. 24፡32) (ሉቃስ 21፡24) አዲሱ እስራኤል ከፖለቲካው እስራኤል የተለየ በክርስቶስ ያመነ ቅዱስ ሕዝብ ነው፡፡

## የማስጠንቂያ ጥሪ (በሲምፕሰን)

ማስጠንቀቂያ ጥሪ በምድር በሰማይ ይሰማል
በዓለም ዙሪያ የወንጌል ጥሪ ይስፋፋል
ኢየሱስ እየመጣ ነው ሰዓቱ ቀርቧል
የወንጌሉ ደወል በዓለም ሁሉ ደርሷል
የማንቂያውን ጥሪ ኃጢአተኛውን
ያለፈው በደል መከደኑን
በክርስቶስ ደም መሻሩን
የመዳን ቀን ዛሬ መሆኑን
የምህረት ወንጌል መልክተኛ እንሁን
ለደከሙ ክርስቲያኖች ደወሉ ይደወል
እንዲመለሱበት በተስፋ ፅኑ ቃል
የመንፈስ ቅዱስ እሳት ይንቀልቀል
የኃጢአት ሸክም ከሕዝቡ ይቃለል
የደውሉን ድምፅ ሚሊዮኖች ይስሙ
ከጨለማው ዓለም ክፉ አይስማሙ
የንጉስ ኢየሱስን ትዕዛዝ እያሰሙ
የአዋጅ ነጋሪ ቃሉን በየቦታ ያትሙ
የደውል ድምፁ ለፈዘዞች ይነገር
ዛሬም በጸጋው ቃል ዘመቻ ይጀመር
የሕዝበ ክርስቲያኑ አይን በሀሰት አይታወር
መናፍስትን መለየት በቅጡ ይጠናከር
በትክክለኛው የክርስቶስ ታምር
ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ የሚያከብር

## ዘመኑን እናስተውል (በዊትሰን)

መቅረዝን በየጊዜው በዘይት መሙላትና በማስተዋል ዘመኑን በመረዳት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው፡፡ ሙሽራው ክርስቶስ ስለሚመጣ አማኞች ዘወትር ተዘጋጅተው እንዲጠባበቁ ጌታ እራሱ ተናግሯል፡፡ "እነሆ ሙሽራው ይመጣል ትቀበሉት ዘንድ ውጡ" (ማቴ. 25፡6)

ዘመኑን ማስተዋልና ጌታን መጠበቅ በዓይናችንና በጆሯችን ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በሁለንተናችን በአስተሳሰባችንና በየእለቱ ኑሯችን ክርስቲያኖች በክብር የሚመለሰውን ጌታን የመጠባበቅ ህይወት እንዲኖረን የሚያሳስብ ነው፡፡ ዘመኑን የሚያስተውል ክርስቲያን በፍቅር የተሞላ በየቀኑ ወደገሀነም በሰይጣን ለሚነዱት ግድ የሚለውና ብዙዎች በክርስቶስ አምነው ከሚመጣው ቁጣ እንዲድኑ የሚጸልይ የሚመሰክርና የሚሰብክ የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡

የሌሎችን ስህተት እየለቀሙ መኮነን የአስተዋይ ክርስቲያን ባህርይ አይደለም፡፡ አስተዋይ ክርስቲያን ሌሎችን ለመኮነን ለማጋለጥ ሳይሆን

የሰይጣንን ክፉ ስራ ለማፍረስ ሌሎችን በፍቅር የሚመክርና ከጥፋት የሚመልስ ሊሆን ይገባዎል፡፡

አንዳንዶች ስለሀሰተኛ አስተማሪዎች የሚያስተምሩትና የሚሰብኩት ስለእውነተኛው አስተማሪ ስለ ክርስቶስ ከሚያስተምሩት ይበልጣል፡፡ በትክክለኛ የክርስትና ትምህርት እውነትን በተገቢው መንገድ መግለፅ የተገባ ሲሆን ሐሰተኞችን መግለጥ የሚገባን ደግሞ ሐሰተኛ ትምህርት ሰዎችን ከእውነተኛው መንገድ የሚያወጣ መሆኑን በመረዳት ነው፡፡

ሐሰተኛ ትምህርትና አስተማሪዎችን እያዩና እየሰሙ በዚህ ዘመን ደግሞ በየሚዲያው ተዕፅኖ እያደረሱ በማየት ዝም ማለት የእነርሱ ተባባሪ መሆን ነው፡፡

የትንቢቱ ቃል ሊፈፀም የግድ ነው፡፡ ሆኖም ግን እኛ ክርስቲያኖች የትንቢቱን ቃል በሚገባ ተረድተን ሰዎች ሁሉ እውነተኛውን ወንጌል በሚገባ ተረድተው ለሌሎች እንዲያካፍሉ ስንተጋ የሀሰተኛ ትምህርቶችና አስተማሪዎችን ስህተትም ለምእመናን በመግለፅ ነው፡፡

ከክፉ ትምህርት ለመጠበቅና በእውነተኛ ትምህርት ለመፅናት ልብን (አዕምሮን) መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

“የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና የአፍህን ጠማማነት ከአንተ አውጣው አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ” (ምሳሌ 4:23)

ማስተዋልና ከክፉ መጠበቅ ሰማያዊ ልማድ ነውና በየዕለቱ በዚህ ቅዱስ ተግባር እንትጋ፡፡

## መጠባበቅና መዘጋጀት (በዳን)

መፅሐፍ ቅዱሳችን ስለመጠባበቅና ስለመዘጋጀት በአስሩ ቆነጃጅት ምሳሌ በሚገባ ያስተምረናል (ማቴ. 25)

አምስቱ ቆነጃጅት ብልህ ሲሆኑ አምስቱ ደግሞ ሰነፎች ናቸው፡፡

ብልሆቹ በሚገባ ተዘጋጅተው ሙሽራውን (ኢየሱስን) የሚጠባበቁ ሲሆኑ ሰነፎቹ ደግሞ ያልተዘጋጁና በሚገባ የማይጠባበቁ ናቸው፡፡

ሰነፎቹ ቆነጃጅት ሙሽራው እንደሚመጣ ቢያውቁም ቅድሚያ የሰጡት ለጊዜያዊ ደስታ በመሆኑ በሚገባ ተዘጋጅተው ሙሽራውን አልተጠባበቁም፡፡ ሰነፎቹ ዘይት ቢኖራቸውም በበቂ ሁኔታ የተዘጋጁ አልነበሩም፡፡ ሰነፎቹ ባላቸው ነገር ብቻ ረክተው ለተጨማሪ ዘይትና በረከት አልተጉም አልፈለጉም፡፡

ብልሆቹ ግን ለወቅቱም ሆነ ለወደፊት በቂ ዘይት እንዲኖራቸው የሚሹና የሚተጉ ሲሆኑ በማናቸውም ጊዜ ሙሽራውን ለመቀበል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

በዚህም ምክንያት ብልሆቹ ሙሽራው በመጣ ጊዜ የደስታው ተካፋይ ሲሆኑ ሰነፎቹ ግን በሩ የተዘጋባቸው ሆነዋል፡፡ ለዘመኑ ክርስቲያኖችም እንዲሁ በቃሉና በጸሎት በየጊዜው የማይዘጋጁና ጌታን የማይጠባበቁ ከመንግስቱ ውጪ ሲሆኑ ዘወትር ተዘጋጅተው የሚጠባበቁ ግን ዘወትር ከሙሽራው ከጌታ ኢየሱስ ጋር ይኖራሉ፤ ይከብራሉ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና ዳግም ምፅአቱን በሚገባ ስለመጠባበቅ ሐዋሪያው ጴጥሮስ የሰጠው በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ቃል እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ “ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለተስፋ ቃሉ አይዘገይም፡፡ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ስለእናንተ ይታገሳል፡፡ የጌታ ቀን ግን እንደሌባ ሆኖ ይመጣል፡፡ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፤ ምድርም በእርስዋ ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል፡፡ ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት

እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል፤ ነገር ግን ጻድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።" 2 ጴጥ. 3:9-14)

## በመንግስተ ሰማይ የሚጠብቀን ተስፋ (በቻርለስ ስፐርጀን)

"በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሳ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለእምነታችሁ ለቅዱሳን ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን" (ቆላ. 1:5)

በሰማይ የሚጠብቅ ተስፋ ምንድን ነው? ይህንን በሚገባ ለማስረዳት አያሌ ስብከትና ትምህርት ያስፈልግ ይሆናል። ሰይጣንና ስራዎቹን የማሸነፍ የድል ተስፋ ለክርስቲያኖች ተሰጥቶናል። የድል ዘንባባ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በእጃችን ውስጥ ገብቷል። የህይወት ጉዟችን ውጣ ውረድና ትግል ከክርስቶስ የተነሳ በተሸናፊነት አይፈጸምም።

በክርስትና ህይወት ድል ማድረግ ብቻ ሳይሆን ብቃትን የማግኘትም ተስፋ ተሰጥቶናል። አንድ ቀን የሚከበንን ኃጢአት ሁሉ በማሸነፍ በአዲስ ህይወት የመኖር ተስፋ አለን። ክበጉ የክርስቶስ ደም ሀይል የተነሳ እቻ የሌለው የእርሱ ህይወትና ፍቅር በሕይወታችን ይገለፃል።

"ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።" (1 ዮሐ. 3:2)

እግዚአብሔርን ፍፁም የምንወድበት ጊዜ ይመጣል። እርሱን ለማገልገል ፍፁም ደስታ የምናገኝበት ወቅት ይኖራል። አገልግሎታችንም ልክ እንደ መላእክት አገልግሎት ብቃት ያለው ይሆናል።

"ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን"(መዝ. ዳዊት 102:1)

ወደዚህ መንፈሳዊ ልምምድ ብንገባ በእኛ ዘንድ ያለመታመን በስህተት መፍረድና ለስጋ ምኞት መገዛት ከቶ አይኖሩም።

በመንግስተ ሰማይ ከሁሉም ክፉ አደጋ የተጠበቅን እንሆናለን ከዚያ ህመም መከራ ሀዘንና ትካዜ ከቶ አይኖሩም።

በመንግስተ ሰማይ አዕምሮን የሚጎዱ ነገሮች አይኖሩም። ጭንቀት የሌለበት የደስታ ዘላለማዊ ህይወት በመንግስተ ሰማይ ይጠብቀናል።

በመንግስተ ሰማይ በዘር በጎሳ በሀይማኖት በቀለም ልዩነት ሳይኖር ሁሉም በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በደስታ ይኖራሉ። ይህ የመንግስተ ሰማይ ተስፋም በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የተጠበቀ ፍፁም ተስፋ ነው። "አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ እጅግ ብዙ ሰዎች" (ራዕይ 7:9)

## "ፈጥኜ እመጣለሁ"

"እንግዲህ በማታ ቢሆን ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮህ ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ" (ማር. 13:35)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ባለቤቱ ብሎ በገለፀልን መሰረት ተመልሶ ስለሚመጣ ተዘጋጅተን በመንፈሳዊ ህይወት እንቅልፋም ሳንሆን ልንጠብቀው ይገባናል።

ከሀሰተኛ ትምህርት ክርስቶስ ከሰጠን ህያው ዘለዓለማዊ ቃልና ከኖረበት ሕይወት ከሚጋጩ የሀሰት አስተማሪዎችና ትምህርታቸው ልንጠበቅ በጣም ያስፈልገናል።

ሰይጣን እራሱን እንደ ብርሃን መልዓክ ሊቀይር እንደሚችል ጌታችን እራሱ ስላስጠነቀቀን በሚታዩ ተዓምራቶችና ድንቆች ተወስደን እንዳንስት እንጠንቀቅ፡፡

በክርስቶስ እንድንፀና ከሚረዱ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናትና ከፀሎት መራቅና ችላ ማለት አይገባንም፡፡

ከሌሎች ጋር መፎካከርና መራራ መሆን አይጠበቅብንም፡፡ ትንሽ ፍቅር ከብዙ ስጦታዎች ይበልጣልና ሁሌም ፍቅር ይኑረን፡፡

ትልቅ ዛፍና ቤት ቀስ በቀስ በምስጥና በብልሽት እንደሚፈርሱ በመረዳት ኃጢአትና ስህተትን በጊዜው ገና በትንሽነቱ በመግታት እናስወግድ፡፡

የስህተት ትምህርትንም እንዲሁ ትንሽ በመሆኑ ወይም ብርቱ የመሰለ ሰባኪና አስተማሪ ስለፈፀመው ቸል አንበል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ከክርስቶስ ቃል ጋር የሚጋጭ ልምምድና ትምህርትን አንቀበል እንራቅ፡፡

በራስ መታመናችንን ጥለን በክርስቶስ ብቻ እንታመን፡፡ እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሁሉ ቢክዱህ እኔ ግን አልክድህም በማለት እንዳንኩራራ እንጠንቀቅ፡፡

እያንዳንዷ እርምጃችንና ህይወታችን ከክርስቶስ ቃልና ህይወት እንዳይጣረስ እንጣጣር በግልፅም ሆነ በስውር በምናደርገው ነገር ሁሉ ጌታ ክርስቶስ አጠገባችን ሆኖ እንደሚመለከተን እናስብ፡፡ "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደስራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" (ራዕይ 22:12)

## በመንፈሳዊ መነቃቃት ዓለምን በወንጌል እንድረስ

በመፅሐፍ ቅዱሳችን መንፈሳዊ መነቃቃትን የሚገልፀው ክፍል ውሃ ወይም ዝናብ በደረቅ መሬት ላይ እንደሚፈስ አይነት ነው፡፡

"በተጠማ ላይ ውኃን በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሽን አፈስሳለሁና መንፈሴን በዘርህ ላይ አፈሳለሁ፡፡(ኢሳያስ 44:3)

"ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ ... እንደዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደመጨረሻ ዝናብ ይመጣል" (ሆሴዕ 6:3)

ህንድና የፓለስታይን ምድር ለኋለኛው ዝናብ ወይም ሞንሱን ለሚባለው ሁነኛ ተጠቃሚ ምድሮች ናቸው፡፡

በብዙ ቦታዎች መሬቱ በውሃ ማጣት ደርቆ በተሰነጣጠቀበትና አቧራ በበዛበት ስፍራ ዝናብ ሲወርድ ልክ እንደትልቅ በረከት ይቆጠራል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም እንዲሁ በክፉ ደረቅ በተጎዱ ቦታዎቻችን አይተናል፤ እናውቀዋለን፡፡

በጃማይካም በእንደዚህ ሁኔታ ምድር ደርቃ የኢትዮጵያው ልዑልና ንጉስ ራስ ተፈሪ ስለደረሰ ከምስጋና በላይ ለራስ ተፈሪ የክርስቶስን ብቸኛ ማዕረግ "የይሁዳ አንበሳ" በስህተት እንደሰጡ ይታወቃል፡፡

በመፅሐፍ ቅዱሳችንም የእግዚአብሔር ጉብኝት ኃጢአትና ችግር በሰፈነባቸው ስፍራዎች ሲክናወን እንደ ልዩ የሰማይ በረከት ይታያል፡፡ "እንደ ዝናብ ... በምድር ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል" (መዝ. ዳዊት 71:6)

መንፈሳዊ መነቃቃት የእግዚአብሔር ጉብኝት በሕዝቦቹ ፀሎትና ንስኃ መከናወን ነው፡፡

"እነሆ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሰ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል፡፡ እናንተ ደግሞ ታገሱ ልባችሁንም አፅኑ የጌታ መምጣት ቀርቧልና፡፡" (ያዕቆብ 5:7)

ብዙዎች የመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ጉብኝት መንፈሳዊ መነቃቃትና የሀሰት ትምህርቶች መስፋፋት ጋር ይምታታባቸዋል፡፡ ነገር ግን በቅዱስ ቃሉ ጌታ እንዳስተማረን ይህ

ሊሆን የግድ ነው፡፡ ጌታ መንፈስ ቅዱስ በሕዝቦቹ ላይ በሀይል ሲሰራ ክፉ መንፈስም በአሳች አገልጋዮቹ ክፋቱንና ማሳቱን እንዲሁ ይቀጥላል፡፡

እኛ ግን መልካሙን ከክፉ በመለየት በወንጌሉ ሥራ እንግፋ (ማቴ. 24፡14፣ ራዕይ 22፡11))

## መልዕክት ከተርጓሚውና አስተባባሪው (አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቴ መካሻ)

***"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከዘለዓለም ያው ነው፡፡" (ዕብራውያን 13፡8)***

የምፅዓቱ የምሥራች በሚል የትርጉም ርዕስ የእንግሊዝኛውን ፅትም ወደ አማርኛ በመተርጎም በሀገር ውስጥና በዓለም ዙሪያ ህዝባችንን እንድንደርስ የረዳንን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን አሜን፡፡

ይህን የትርጉም ሥራ በሀገር ቤት ሳለሁ ለአስራ አንድ ዓመታት ከሀገር ቤት ከወጣሁ ለአስራ አራት አመታት በድምሩ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ሳገለግል ቅዱስ መንፈሱን ከእኔ ያላራቀ ከክፋትና ውድቀት እኔንም ሆነ ተባባሪ አገልጋዮቼን ውድ ባለቤቴን ፋንታዬ ግርማን፣ አስተባባሪዋን አልማዝ አሳየን ያቆመን ክርስቶስ ክብር ምስጋና ውዳሴ ይድረሰው፡፡

በዚህ አገልግሎት ስለተፅናኑት ወደ ክርስቶስ እምነት ስለገቡትና ከውድቀት ስለተረፉት ሁሉ ምስጋናና ክብሩ ለክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ይሁን፡፡

ከቀድሞው ብስራተ ወንጌል ጀምሮ በመገናኛ ብዙኃን ቅዱስ ወንጌሉን ላሰራጩት ሁሉ ጌታ ይባረክ፡፡ እነርሱንም አብዝቶ ጌታ ክርስቶስ ይባርካቸው፡፡

የመገናኛ ብዙኃን ለቅዱስ የእግዚአብሔር ሥራም ሆነ ለክፉው የዲያቢሎስ ስራ መሳሪያ ሊሆኑ ስለሚችሉ ቅዱሳን ክርስቲያኖች ሁሉ መገናኛ ብዙኃንን ክርስቶስ እንዲነግስባቸው ልንፀልይ፣ ልንመሰክርና ልንደግፍ ይገባል፡፡

ከአስራ አራት አመታት በኋላ ወደ ትውልድ ሀገሬ ኢትዮጵያ ለጉብኝት ተመልሼ ስላየሁት መንፈሳዊ እድገት ኢኮኖሚያዊ መሻሻል ጌታን እያመሰገንኩ በጎደለው ሁሉን ቻይ አምላክ እንዲሞላ እፀልያለሁ፡፡በሚቻለኝ ሁሉ በጎ ነገሮች በኢትዮጵያ እንዲስፋፉ ከውድ ባለቤቴ፣ ልጆቼና ተባባሪዎቼ ጋር እጥራለሁ፡፡

አሁንም ለአገልግሎቱ መቀጠልና መሻሻል ፀሎታችሁና ድጋፋችሁን በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን፡፡

*የምፅዓቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ*

# ዓለም አቀፍ የፀሎት ርዕሶችና ምስጋናዎች

## ከባቢሌ ምስራቅ ኢትዮጵያ

በምስራቅ ኦሮሚያ (ኢትዮጵያ) ወንጌሉን ለሚያሰሙ ወገኖች ሁሉ አብዝተን እንፀልይ፡፡ አንዳንዶች የሚደርስባቸውን ዛቻና ጫና ሳይፈሩ ለሚተጉ ወገኖቻችን በፀሎትም በገንዘብም እንደግፋቸው፡፡

## ከባህር ዳር ሰሜን ኢትዮጵያ

የተለምዶ የክርስቲያን አካባቢ ተብለው ለሚታወቁት ለአጠቃላዩ የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍሎች ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛው አዳኝና ጌታ መሆኑን እስኪያውቁ ድረስ ለመሪዎችና ለሕዝቦቻችን ብርቱ ፀሎት እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡

## ለመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ

በመላው ዓለምና በሀገራችን ኢትዮጵያ ጭምር መፅሐፍ ቅዱስን ለሚተረጉሙና ለሚያሰራጩት ሁሉ በብርቱ እንፀልይ፡፡

## ለክርስቲያኖች አንድነት

በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑት ሁሉ እንደ በአለ ሀምሳ (ጴንጤቆስጤ) እለት በአንድ መንፈስ አንድነት እንዲኖራቸውና ዓለምን ሁሉ እንዲደርሱ እንፀልይ።

## ለፓኪስታን ክርስቲያኖች

በየጊዜው በፊንጂ ጥቃት ለሚደርስባቸው ይህ ሳይበግራቸው ለክርስቶስ ወንጌል የሚተጉትን የፓኪስታን ክርስቲያኖችና ሚሲዮናውያን ጌታ እንዲጠብቅ እንፀልይ፤ በሚቻለንም እንርዳ።

## በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ እንፀልይ

በቅርቡ በደቡብ አሜሪካ በኢኳዶርና በሌሎችም ቦታዎች በመሬት መናወጥና በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ለተጠቁት እንፀልይ። በዚህ መሰሉ አደጋ ለተጎዱትም የምንችለውን እንለግስ።

## ለመሪዎች ፀሎት

በቅዱስ ቃሉ በታዘዝነው መሰረት በየሀገሩና አህጉራቱ ላሉ መሪዎች ሕዝቦቻቸውን በፍቅር ያለአንዳች ልዩነት እንዲያስተዳድሩ እንጸልይ።

"ልመናና ፀሎት ምልጃም ስለመኳንንትም ሁሉ እንዲደረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ" (1 ጢሞ. 2:2)

*የምጽዓቱ የምሥራች ዓለም አቀፍ የወንጌል መነቃቃት*
*አሳታሚ፦ ሪክ ካርማይክል*
*ተርጓሚ፦ አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቴ መካሻ*
*በኢትዮጵያ ተወካይ፦ አልማዝ አሳየ*
*የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ*
*ኮምፒተርና ዲዛይን*
*አቤኔዘር የዕህፈት ሥራ*
*መካኒሳ አዲስ አበባ*

# ለሁሉም ሰው የመዳን ምክሮች

1. ኃጢአተኛ ለመሆናችን ንስሀ ገብተን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ጌታና አዳኝ አድርገን እንቀበለው። (ዮሐንስ ወንጌል 1:12)
2. በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም ከሚያጠምቁ አጥቢያ ማህበረ ምዕመናን ዘንድ አባል እንሁን። (ማቴዎስ ወንጌል 28:19)
3. ይህን የተቀበልነውን የመዳን ዕውቀት በልባችን አምነን በአፋችን ለሰዎች ሁሉ በመመስከር በህይወት እንፅና።(ሮሜ መልዕክት 10:9)
4. መንፈስን ሁሉ አትመኑ። ከዚህ እውነት የተለየ ከሚያስተምሩ ሀሰተኞች ራቁ። (1ኛ ዮሐንስ 4)